# Sudan farmers get back disputed lands from Ethiopia

Sudan Tribune



July 5, 2007

**KHARTOUM, Sudan - A joint Sudanese-Ethiopian committee would start today to hand over agricultural lands to residents of more than 17 Sudanese villages located in eastern Atbara River along the Ethiopia-Sudan border.**

**የሚቀጥለው ግጥም የጊዚው መንግስት የኢትዮጵያን ሕዝብ ሣያማክር እንደፈለገ የኢትዮጵያን ዳር ደንበር ሥለሚያሸናሽን ድርጊቱን በመቃወም ይተጻፈ ነው።**

**ወይ ፍርድ ማስተካከል አወይ ሃብት መገንባት**
**የኢትዮጵያን ንብረት በጎሣ ተመናት።**
**አገሬ ኢትዮጵያ ምኑን መርዝ ጠጣሽው**
**እርሃቡሥ ቢብዛ ምኑን መርዝ በላሽው**
**ለቀብር ዳርጎሻል ከሆድሽ የወጣው።**
**ምነው በተገኘሽ እትየ ጣይቱ**
**ዛሪም እንደገና ሕዝብ ሳያማክሩ**
**ደንበር ሲያቃርጡ።**
**አገሪ አትዮጵያ ጎጤ በጌምደር፤**
**በፍጹም አልፈቅድም**
**ደንበር እንዲያናጋ ሕዝብን ሳያማክር።**
**አቤት! አቤት! አቤት!**
**ስማኝ ወዶ ገነት፤**
**አዲሱ መዋቅር ጨረሰ ወይ እንጨት**
**ለማገዶ አዞዋል አፈርና ኩበት።**
**ፎገራ አዲስ ዘመን በሕልሜ እንዲህ አለኝ፤**
**አይዞሽ አትደንግጭ ይልቅስ መዝግቢ**
**አጥንት ደም ፈሶዋል ለኢትዮጵያዊነት**
**መፋረድ አይቀርም ጊዜ የመጣ ለት።**

አዳምጠኝ መቀሌ ሊላው ይቅርና
የኢትይጵያ ልጆች
ለዳር ደምበር ሲሉ
ጋራ ሸንተረሩን በግልጽ አትምውል
እርሳስ ደብተር ሳይኖር
ደማቸው ነው ቀለም ፊታቸው ብራና፤
ከቀብርም ይጠራል
እንፋረድ ብሎ ደሽ ቀን ይለፍና
አዳምጠኝ ወልቃይት ሌላው ይቅርና።
ምነው በተገኘሽ እትየ ጣይቱ
ዛሪም እንደገና ሕዝብን ሳያማክሩ
ደንበር ሲያቃርጡ።
ጎንደር ፋሲለደስ በሕልሜ እንዲህ አለኝ፤
ሂጅ ተናገሪ አደራ የኔ ልጅ
መዋረድ አይሆንም ለሐገር መሞዋገት
ነውርም አይደለም መባል ኢትዮጵያዊት፤
የ አያቶችሽ ደም ነው ያቆየልሽ እርስት።
ስለዚህ አደራ መለስ ከለስ አርገን
ይህን እንጠይቃለን
አገሪ ኢትዮጵያ ምን መርዝ አብቅለሻል?
ያኔ የበላሽው የአድዋ ፍሪ እህል
ለቀብር ዳርጎሽል።
አዳምጠኝ መቀሌ ሊላው ይቅርና
ይህን ሰምቻለሁ ከኢትዮጵያ ልጆች
አዳምጠኝ ወልቃይት ሌላው ይቅርና፤
እንፋረድ ሲሉ እውነቱ ይውጣና።
እኔም እንደነሱ ቃል ኪዳኔ ይህ ነው
አገሪ አትዮጵያ ጎጤ በጌምደር፤
በፍጹም አልፈቅድም
ደንበር እንዲያናጋ ሕዝብን ሳያማክር።

©ለምለም ጸጋው፤
July 6, 2007